ከደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት በፈረንሣይ ፓሪስ ከተማ በሚካሄደው
<u>የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ስብሰባ የቀረበ መልዕክት</u>

በኢትዮጵያ ዘመናዊ የመንግሥት አስተዳደር ሥርዓት ከተዘረጋበት ጊዜ አንስቶ በርካታ የመንግሥትና የሥርዓት ለውጦች ተካሂደዋል። በእነዚህ የለውጥ ሂደቶች አንዱ ሥርዓት ሌላውን እየተካ ይለፍ እንጂ የተሟላ ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ሊመጣ አልቻለም። የመንግሥትና የአስተዳደር ሥርዓቶች ግን ሲቀያየሩ ኑረዋል። በመንግሥት መቀያየር ወደ ሥልጣን የሚወጡ ቡድኖች የተሣሣተ ሕዝባዊና ሀገራዊ ፖሊሲዎችን ሲከተሉ ቆይተዋል።

በፊውዳሉ ሥርዓት የነበሩት የአስተዳደር ግድፈቶች በ1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ አብዮት ቢወገዱም፤ ውጤቱን የደርግ አምባገነን አመራር አጨናግፎታል። ወታደራዊ ደርግን የተካው የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) በባለተራነት የመንግሥት ሥልጣን ከያዘ በኋላ በታላቅ ጉጉት ሲጠበቅ የነበረውን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምሥረታ አደናቅፎታል። በአፉ "ከእኔ ወዲያ ዴሞክራት፤ የብሄረሰቦች ችግር ፈቺና የጭቁኖች ወገን የለም" እያለ ፕሮፓጋንዳውን ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ እያሰራጨ በተግባር ግን ተቃራኒ ድርጊት እየፈፀመ ይገኛል።

ከላይ በአጭሩ እንደተመለከተው የሀገራችን መሠረታዊ የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ፤ እንዲሁም የብሄረሰቦች የመብት ጥያቄ ገና ያልተፈታ መሆኑን ነው። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ትልቁ የፖለቲካ ችግር ሆኖ የቆየው የብሄረሰቦች ሁለገብ የመብት ጥያቄ፤ ማለትም የደርግ ሪጅናል ኦቶኖሚ ወይም ወደ ኋላ ወደ ራስ ገዝ ከወረደው ጀምሮ እስከ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ፌዴራሊዝም ድረስ፤ ወረቀት ላይ ተጽፎ ከመታየቱ አልፎ ተግባራዊ ምላሽ ሳያገኝ ቀጥሏል።

<u>ሀ. የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት (ደኢሕዴኅ) እንቅስቃሴ</u>

ዛሬ ደቡብ ኢትዮጵያ ብለን የምንጠራው የሀገሪቱ ክፍል ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት ብሄር/ብሄረሰቦች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የሚኖሩበት ነው። እነዚህ ብሄር/ብሄረሰቦች እስከ ዛሬ ድረስ ሕልውናቸው ተረጋግጦና ብሄራዊ መብቶቻቸው ታውቆ በሀገሪቱ ውስጥ በሚካሄዱት ማኅበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፓለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሚና እንዳይኖራቸው ተደርገው ኑረዋል። ሁልጊዜም ወደ ዳር እየተገፉ ናቸው። ራሣቸውን በሚመለከታቸው ጉዳዮች እንኳን በተገቢው ቦታና ጊዜ ድምፃቸውን እንዳያሰሙ ሲነፈጉ ቆይተዋል። ባጭሩና በተጠቃለለ አባባል ድምፅ የሌላቸው (Voiceless) ነበሩ። በኢትዮጵያ ሕዝቦች ስም ለፖለቲካ ጠቀሜታ ሲባል ብዙ ቢለፈፍና አንዱና ብቸኛው ለችግሩ መፍትሄ ሰጪ ነን የሚሉ ወገኖች መነሣታቸው ቢታወቅም የደቡብ ሕዝቦች የመብትና ጥቅም መከበር ጉዳይ እስከ ዛሬ ድረስ ሁነኛ ምላሽ አላገኘም።

የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት (ደኢሕዴኅ) በቅርፅ ክልላዊ የፖለቲካ ድርጅት ቢሆንም በይዘት ግን ከ46 በላይ ብሄር/ብሄረሰቦችን የሚወክል ከመሆኑም በላይ 15 ያህል የብሄር/ብሄረሰቦችና ክልላዊ አጀንዳ ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶችን ያካተተ ኅብረት ነው። በገዛ ሀገራቸው ስለራሣቸው ለመናገር ዕድል ተነፍገው ለዘመናት ተገልለው ስለሚኖሩ ሕዝቦች ጉዳይ በማንሣት ተገቢና ሞራላዊ ኃላፊነትን እየተወጣ ያለ ድርጅት ነው።

በ1985 ዓ.ም. በተካሄደው የፓሪስ ጉባዔ ላይ በመሣተፉ የተነሣ በጊዜው ከነበረው የሽግግር መንግሥቱ ም/ቤት 17 መቀመጫዎች የነበራቸው 10 የደኢሕዴኅ አባል ድርጅቶች በኢሕአዴግ አምባገነናዊ ውሣኔ ም/ቤቱን ለቅቀው እንዲወጡ ተገደው ነበር። ከዚያም በኋላ ደኢሕዴኅ በሀገር ቤትና በውጭ ያለውን የተቃዋሚዎች እንቅስቃሴዎችን ለማስተባበር ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። በዚሁ መሠረት ከታኅሣሥ 9-13/1986 ዓ.ም. በግዮን ሆቴል የተካሄደውን "ሠላምና ዕርቅ በኢትዮጵያ ሀገር-አቀፍ ጉባዔ" በማዘጋጀት ከፍተኛ መስዋዕትነት መክፈሉ የማይዘነጋ ተግባር እንደነበር ለሁላችንም ግልጽ ነው። ዛሬ በሀገራችን የፖለቲካ መድረክ ላይ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ላለው የኢሠዴአኃ ም/ቤት መቋቋምና ቀጣይ እንቅስቃሴው አስተዋጽኦ በማድረግ ሀገራዊና ሕዝባዊ ግዴታውን የተወጣ እና እየተወጣም የሚገኝ ድርጅት ነው።

ይህ አሠራሩና አካሄዱ የትግል አድማሱና ዓላማው በተወሰነ ክልልና ብሄረሰብ ተገድቦ አለመቅረቱን ያረጋግጣል። በመሆኑም ደኢሕዴኅን "የጎሣ ድርጅት" እንደሆነ አድርገው ለማቅረብ የሚሞክሩ ግለሰቦችና ቡድኖች ስለ ድርጅታችን አቋም የማያውቁ ወይም አውቀውም ቢሆን አመዛዛኝ አስተያየት የሌላቸው ናቸው። እነዚህ ወገኖች ሀገር በተወሰኑ ቡድኖች ብቻ እንደሚቋቋም አድረገው የሚያስቡ ናቸው። ራሣቸውንም ለሌላው ወገን ስያሜና ዜግነት ደልዳይ አድረገው የሚያዩና ከእነሱ ሌላ ለኢትዮጵያ ታማኝና ተጠሪ እንደሌለ አድርገው በአደባባይ የሚቀርቡ ናቸው። የሀገሪቱ ባለአደራ እኛ ብቻ ነን ማለትም ይቃጣቸዋል። ሀገሪቱ የምትኖረው በእነሱ ታጥራ እንደሆነና ሌሎች ሕዝቦች ደግሞ የአንድነት ግንቡን አፍርሰው በሄዱበት ያለ እረኛ

እንደተሰማራ መንጋ ተበትነው እንደሚቀሩ ይሰማቸዋል። ይህ [redacted] የአንዳንድ ወገኖች አመለካከት ለሀገራችን አንድነትና ሕልውና የአደጋ ምንጭ እንደሆነ ደኢሕዴኅ ማስገንዘብ ይወዳል።

የኢትዮጵያ ብሄር/ብሄረሰቦች የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚያተኩረው የተነፈጉትን መብት በራሣቸው ትግል ማስመለስ እንደመሆኑ የደቡብ ኅብረት ዓላማም ይኸው ነው። ከሌሎች ወገኖች በጎ ምላሽና የትግል ትብብር የምንሻ ቢሆንም እንተካችሁ የሚሉትን ወይም ለሰብዓዊ ክብራችንና ብሄራዊ መብታችን የምናደርገውን ትግል የሚያንኳስሱ ወገኖችን ተግባርና ዓላማ የምንታገለው መሆኑን ሁሉም ወገኖች እንዲያውቁት እንሻለን።

እጅግ ሲበዛ ድሃ በሆነችውና አምባገነን መሪዎች በሚፈራረቁባት ኢትዮጵያ ሀገራችን፤ ከዳር ቁጭ ብሎ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት መጠበቅ ተላላነት ነው። ይህን አስከፊ ገጽታ ለመለወጥ ሕዝብን ማስተማርና ማንቃት የሚችል ብቃት ያለው የፖለቲካ ድርጅት በመፍጠር በሠላማዊ ትግልና በሕዝባዊ ምርጫ አምባገነኑን መንግሥት ለመተካት፤ ብሎም የደቡብ ሕዝቦችን ፖለቲካዊ ሚና ለማጎልበት ደኢሕዴኅ እንቅስቃሴውን ከጀመረ 6 ዓመታት አልፈዋል።

ደቡብ ኅብረት ከተመሠረተበት ማግሥት ጀምሮ በሚወክለው ሕዝብ ክልልና በሌሎችም የደቡብ ሕዝቦች በብዛት በሚገኙባቸው ከተሞች ቅ/ጽ/ቤቶችን፤ በአዲስ አበባ ደግሞ ዋና ጽ/ቤት ከፍቷል። በአዲስ አበባ፤ በሀድያ- ሾኔ ከተማ፤ በሰሜን ኦሞ ዞን በአርባ-ምንጭ ከተማ በትግላችን የከፈትናቸው ጽ/ቤቶች በመሥራት ላይ ሲገኙ በሚደረግብን ከፍተኛና ሁሉ-ገብ ተፅዕኖዎች ምክንያት በቀሩት ቦታዎች የነበሩት ግን እንደተዘጉ ናቸው። ወደፊት እንደገና በእነዚህና እንዲሁም በሌሎች ቦታዎች ጽ/ቤቶችን ለመክፈትና በስፋት ለመሥራት ዝግጅቱ አለን።

የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት በአምባገነንነቱ ከዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች ጋር ተወዳድሮ ማሸነፍ እንደማይችል ስለተረዳ፤ በተለያየ ጊዜና በተለያየ ደረጃ ካደረጋቸው የምርጫ ፕሮግራሞች፤ ደቡብ ኅብረትን ለማግለል እልህ አስጨራሽ ተፅዕኖ ማድረጉን ባያቋርጥም፤ ቀደም ባሉ ጊዜያት በተደረጉትና በቅርቡ በታኅሣሥ/1990 ዓ.ም. በተደረገው በደቡብ የወረዳ ምርጫ ለሙከራ ያህል ተወዳድረን በተወሰኑ ወረዳዎች አሸንፈናል። ይህም "ሁሉም በእጄ ሁሉም በደጄ" ብሎ የተነሣውን ሕወሓት/ኢሕአዴግን በምርጫ ልናሸንፈው ወይም ልናንበረክከው እንደምንችል ከማሣየቱም በላይ፤ እኛም ጥሩ ልምድ ያገኘንበትና ሕዝባችንም ለበለጠ ትግል እንዲበረታታ ያደረግንበት አጋጣሚ ነበር። በተሣተፍንባቸው ምርጫዎች አማካይነትም የሕወሓት/ኢሕአዴግን ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ምርጫ አቋም ለሦስተኛ ጊዜ ለማጋለጥ ችለናል። እንዲሁም ሁሉም የተቃዋሚ ፖለቲካ ኃይሎች በምርጫው እንዲሣተፉ የሚያስችሉ የዴሞክራሲያዊ የምርጫ ቅድመ-ሁኔታዎች እንዲሟሉና የፖለቲካ እሥረኞች እንዲፈቱም ጭምር በመጠየቅ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ከገዥው መንግሥት ጋር ለመደራደር ሞክረናል። ሕወሓት/ኢሕአዴግ በዚህ በኩል በጎ ምላሽ ያልሰጠ ቢሆንም በምናደርገው ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ የተዘጋውን በር ለማስከፈት እንችላለን የሚል እምነት አለን።

<u>ለ. የሕወሓት/ኢሕአዴግን አስተዳደር ሥርዓት በተመለከተ</u>

የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት በግትርነቱ የተለያየ የፖለቲካ አመለካከት ካላቸው ሠላማዊ ወገኖች ጋር መወያየት የማይፈልግ፤ መንግሥታዊ ኃላፊነትና ተጠያቂነት በአግባቡ ያልተወጣ አምባገነን ነው። በሽግግሩ ወቅትም ሆነ በምርጫ ሥልጣን ይዣለሁ ብሎ ማስመሰል ከጀመረበት ጊዜ ወዲህ ያወጣቸው የአገር ውስጥና የውጭ ግንኙነት ፖሊሲዎቹ በብዙ መልኩ እምነት የሚጣልባቸው ሆነው አልተገኙም። በዚህም እመሠርታለሁ ብሎ ሲምል-ሲገዘትለት የነበረውን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፤ ፍትሃዊ አስተዳደርና ሠላም በገዛ ደንቃራነቱ አጨናግፎታል።

አንድ መንግሥት ውስጣዊ ባሕሪውና ጥንቅሩ ፖሊሲውን የሚወስን በመሆኑ ሕወሓት/ኢሕአዴግ በአገር ውስጥ የሚከተለው የተዛባ የአስተዳደር ዘይቤው አገሪቱን ከድጡ ወደማጡ እየወሰዳት ነው። ከርዕዩተ-ዓለም መሠረታቸው መነሻነት ከፋፍለህ-ግዛ የአስተዳደር ሥልት ባለመላቀቃቸው የተነሣ፤ ከሽግግሩ ዘመን ጀምሮ በሕዝብ ላይ የተፈፀመው በደል እንዲህ ቀላል አይደለም። እጅግ መራር የሕዝብ ግጭቶችና እልቂቶች ተፈጽመዋል። ለምሣሌ ዎላይታ አርካ ላይ ተርበው እርዳታ ለመለመን በወጡ ወገኖች ላይ ከፍተኛ የኃይል እርምጃ ተወስዷል፤ ብዙ ሰዎች ተገድለዋል፤ ቆስለዋል። በጋሞ-ጎፋ፤ በጋሞ ብሄረሰብ አባላትና ዎላይታ ነዋሪዎች መካከል የፈጠሩት ተቀጣጣይ አምባጓሮ የደም መፋሰስን አስከትሏል። በዚሁ አካባቢ አርባ-ምንጭ ከተማ በኦርቶዶክስና ፕሮቴስታንት ኃይማኖት ተከታዮች መካከል ሆን ተብሎ በተጫረ ግጭት አስነዋሪ በደሎች ተፈጽመዋል። ለ3 ቀናት ከተማው ገላጋይና አስተዳደር አልባ ሆኖ ከርሟል። ሴቶች መዘምራን ተደፍረዋል። ቤተክርስቲያናት ተቃጥለዋል። ለ3 ቀናት ያህል ቤት-ለቤት የተካሄደ ዘረፋ ተደርጓል። በተመሣሣይ ሁኔታ በአ/አበባ፤ ወሊሶ፤ ጎንደርና በሌሎች ቦታዎች በኃይማኖት ሰበብ የተፈጠሩት ግጭቶች ያስከተሉት አስፀያፊና ጎጂ ውጤቶች በትዝብት የሚታወሱ ናቸው። የኮንሶና ዴራሼ ብሄረሰቦች ተጋጭተው ሕይወትና ንብረት በማይታሰብ መጠን ወድሟል። የፃማይ ዘላኖች (ከብት አርቢ ገበሬዎች) መሬታቸውን አንለቅም በማለታቸው

በመንግሥት ታጣቂዎች አሸባሪነት ሕዝቡ ከመሰደዱም በላይ፤ አቤቱታ አቅራቢ የሕዝብ ተወካዮች ሲገደሉ ከሟቾቹ ውስጥ አራቱ የአንድ ቤተሰብ አባላት ነበሩ።

ኮይራ (ኮሬ ልዩ ወረዳ) ከፊሉ ሕዝብ ጋሞ-ጎፋ አስተዳደር እንመለስ በማለቱ ብቻ ይህንን ባልደገፉት የወረዳው አስተዳደር ኃላፊዎች ጥቆማ ከመንግሥት በተላኩ ወታደሮች ሕዝቡ እንዲመታ ተደርጓል። የሞተው ሞቶ፤ የቀረው ላለፉት 4 ዓመታት ታሥረው ይገኛሉ።

በሀድያና ጉራጌ መካከል የተነሣው የመሬት ወይም ቀበሌ ይገባኛል ጥያቄ ብዙ የሕይወትና ንብረት ጉዳት አድርሶ አካባቢውን ሁለቱም ወገኖች በመፈራረት ለቀው በመውጣታቸው ቀበሌው ነዋሪ አልባ እስከ መሆን ደርሶ ነበር። ይሄም ሕዝብና ቅዬው መካከል በክልል ጉዳዩና በሃይማኖት ሳቢያ 11 ሰዎች እስከ ኢ.ለበጣቸው መንገድ ታርደው [illegible] ሕፃናትና አረጋዊያን ሳይቀሩ ከእምነታቸው ተደርገዋል።

በቅርብ ጊዜ በጌዴኦና በጉጂ-ኦሮሞ መካከል ከሐምሌ 15 ቀን 1990 ዓ.ም. ጀምሮ የተነሣውን ግጭት ሁሉም ወገን በቅርብ የሚያውቀው ነው። የግጭቱ መነሻ የሆነው አሁንም የግዛት ወይም የክልል ጥያቄ የሚባለው ሲሆን፤ የሕወሐት/ኢሕአዴግ አመራር በሌላው ክልል የሚኖሩ የክልሉን ብሄረሰብ የማይመስሉ ከሆነ "መሬቱን ይዘው ወደ ብሄረሰባቸው (የቀድሞ ክልላቸው) ይመለሱ" የሚል ፖሊሲ የሕዝቡን ፍላጎት ያላካተተ በመሆኑ የተነሣ ግጭት ነበር። የጀብደኛ የኢሕአዴግ ካድሬዎች ቅስቀሣም ለግጭቱ መነሣሣት ምክንያት ሆኖአል። በሠላም አብረው ከትውልድ ትውልድ የኖሩትን ሕዝቦች የኢሕአዴግ የተሣሣተ ፖሊሲ ሕዝቦቹ ደም እንዲቃቡና ንብረታቸው እንዲወድም አድርጓል። በግጭቱ ከ3000 በላይ የሚሆኑ ወገኖቻችን እንደሞቱ፤ ከ16000፬ በላይ ሰዎች እንደተፈናቀሉ ይገመታል። ቤቶች እንደተቃጠሉ፤ በብዙ ሚሊዬን ብር የሚገመት ንብረት፤ ቡና፤ እንሰትና ሌሎች ተክሎች እንደወደሙ መረጃዎች ያረጋግጣሉ።

በነፃ ተዘዋውሮ መረጃዎቹን ለማሰባሰብ ካለመቻሉም በላይ፤ የደቡብ ኅብረት አባላት መረጃ አሰባሰባችሁ ለነፃው ፕሬስ ታስተላልፋላችሁ በሚል ምክንያት ይንገላታሉ፤ ይታሠራሉ። ተጎጂዎቹም ቢሆኑ በነፃ ለመንቀሣቀስና እርዳታ ለማግኘት አልቻሉም። እንዲያውም መንግሥት ወደ ቀድሞ ቦታቸው እስካልተመለሱ በስተቀር እርዳታ እንደማይሰጣቸው አሣውቋል። በግዴታና ኃይል በታከለበት እርምጃ ነፍሴ አውጪኝ ብሎ የተሰደደው ሕዝብ በቀድሞው ቦታ ተመልሶ እንዲሰፍሩ እያደረገ ነው። ከሁሉም አስቀድሞ ሰብዓዊ እርዳታ ማቅረብና የዜጎች ደህንነት እንዲጠበቅ ማድረግ ሲገባው፤ አሁንም ወደተሰደዱበት ቦታ ተመልሰው እንዲሰፍሩ ከማስገደድ ባሻገር ስለተፈጠረው ግጭትና ስላስከተለው ችግር አንዳችም ይፋ መግለጫ መንግሥት አልሰጠም። እንዲያውም በተዳፈነ ሁኔታ ቆይቶ እንዲቀር ወይም እንዲዘነጋ ከፍተኛ የመከላከልና የእንቅስቃሴ እገዳ አድርጎ ከቆዩ በኋላ፤ አፈናው ሲጋለጥበት ደግሞ "አስታርቄአለሁ" የሚለውን ድራማ በቴሌቪዥን መስኮት አሣይቷል።

ከዚህ ጋር አብሮ መነሣት ያለበት በሌሎች ክልሎች በኦሮሚያ የበደኖ፤ የወተር፤ በጅማ አካባቢ የየምና የኦሮሞ፤ በአርሲ በአርባ-ጉጉ እንዲሁም በቤንሻንጉል ክልል በፓዌ ዞን የተፈፀመው የኃይል እርምጃ በደቡብ ከተከሰቱት ጋር ተመሣሣይነት እንዳላቸው ነው። ይህንን ሁሉ ለጊዜ ፍርድ ትተን ማለፍ ብንመርጥም፤ ዛሬ ትኩስ ጉዳይ ሆኖ በቀረበው ጌዴኦና ጎጂ-ኦሮሞ ላይ ስለደረሰው ሰቆቃ ውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ሁለገብ ድጋፍ እንዲያደርጉና ለዓለም ማኅበረሰብ ማሰማት ይጠበቅባቸዋል።

ለማጠቃለል ሕወሓት/ኢሕአዴግ እንደ መንግሥት ሕግንና ሕጋዊነትን ተከትሎ የሚሠራ ተአማኒነት (credibility) ያለው መንግሥት ያለ መሆኑን የእስከአሁን አመራሩ አሣይቶናል። ይህ ቡድን አሁንም በጫካው የወያኔ ፖሊስ የሚመራ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ሁሉን ተጠራጣሪና ለገዛ-ፍላጎቱ ብቻ የቆመ ቡድን ነው። ያለውንና የፈለገውን ለመፈፀም ሲባል ብቻ እጁን የማይዶልበት ቦታና ጉዳይ የለም።

ሐ. <u>በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል ስለተከሰተው ግጭት</u>

የዚህ ግጭት መነሻ ባለብዙ ፈርጅ ምክንያቶች ያሉት ነው ቢባልም በመጨረሻው ሰዓት የሁለቱ ጦርነት ሰበብ የድንበር ግጭት ሆኖ ተከስቷል። ይህ የድንበር ግጭት በብዙ ወገኖች የኢትዮጵያን መንግሥት ጨምሮ የኢትዮጵያ የሉዓላዊነት መደፈር ወረራ ሆኖ ተወስዷል። ይህ ክስተት የወጭ ኃይል ወረራ የመሆኑ ጉዳይ በመንግሥት መገናኛ ብዙኃን ተደጋግሞ ተገልጿል። በሌላ በኩል ክስተቱ የድንበር ግጭት ተባለም ወረራ፤ ፍሬ-ነገሩ ተመዞ ሲወጣ ሁለት መሠረታዊ ነጥቦችን ማየት ይቻላል።

1. የኤርትራ ጥያቄ አሁን በጦር ኃይል የያዘው ግዛት ጉዳይ ብቻ ከሆነ በሠላማዊ መንገድ ችግሩ እንዲፈታ ይፋ ጥያቄ ማቅረብ ይቻል ነበር፤ ግን ኤርትራ ጦርነት ጀማሪ ከመሆኑም በላይ ያንዱን ነፃ አገር ዳር-ድንበር ጥሷል። የኢትዮጵያ የግዛት አንድነት ተጥሷል፤ አገራዊ ሉዓላዊነትም ተደፍሯል። እንደዚሁም ጦርነቱ በተጀመረበት አካባቢ ይኖሩ የነበሩት ኢትዮጵያዊያን በወታደራዊ ኃይል ተጠቅተዋል፤ ተገለዋል፤ ተጎድተዋል፤ ንብረታቸውም ወድሟል።

2. በማጥቃቱም ጊዜ ሆኖ በመልሶ ማጥቃት ጦርነት ጊዜ ከፍተኛ የሰው ሕይወትና ንብረት ጠፍቷል። ባጭሩ ኤርትራና ኢትዮጵያ መካከል በተጫረው ጦርነት በአካባቢው ሠላም ደፍርሷል፤ ከፍተኛ ንብረትና ሕይወትም ወድሟል።

ይህ የሁለቱ አገሮች ጦርነት አቢይ ምክንያት ከላይ እንደተጠቀሰው ቢሆንም የሕወሓት/ኢሕአዴግ የተዛባ የኢትዮ-ኤርትራ ግንኙነት ፖሊሲ ለግጭቱ ሰፊ አስተዋጽኦ አድርጓል። ኤርትራ ነፃ ወጥቻለሁ ካለችበትና በሕወሓት/ኢሕአዴግ የሚመራው የኢትዮጵያ መንግሥትም ነፃ አገር አድርጎ ከተቀበለ ጊዜ ጀምሮ በሁለቱ ሀገሮች መካከል የሚደረገው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ሚዛናዊ አልነበረም። ሲበዛ ለኤርትራ ያደላ፤ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም የማያስጠብቅና የመንግሥት ኃላፊነት የተጓደለበት ግኑኝነት ነበር።

በሥልጣን ላይ ያለው የወቅቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ለሀገራዊ ኃላፊነትና ብሎም ለተጠያቂነት ብዙም የማይጨነቅ መሆኑ የታወቀ ነው። የዚህ ዓይነቱ ከዓለም የሀገሮች ግንኙነት ሥርዓትና ልምድ ያፈነገጠ አሠራር ያስከተለው ግጭት እንደሆነ እናምናለን። የወቅቱ የኢትዮጵያ ገዥዎች የኤርትራን ነፃነት ሲቀበሉ፤ የሁለቱ ሀገሮች ድንበር ዬት ሆኖ ነበር? ዜጋውስ ማነው? የሚሉትን ጥያቄዎች በጊዜውና በአግባቡ መመለስ ነበረባቸው። ሰበቡ የድንበር ጥያቄ ይባል እንጂ ሌሎች በግልጽ ያልተነገሩ የጥቅም ግጭቶችም ያሉበት ስለሆነ ይፋ ጦርነት ከተነሣ በሁለቱም ወገኖች የሚደርሰው ጉዳት እጅግ የከፋ ይሆናል። ስለሆነም ጉዳቱ ሰፍቶ የሀገራችን ሠላምና ፀጥታ ጨርሰውኑ እንዳይናጋ ከወዲሁ ሊታሰብበት ይገባል። ይህን በሕዝብ ላይ ሊደርስ የሚችለውን መከራ በአጭሩ ለመቅጨትና ለማስቀረት ሁለቱ ሀገሮች የሚከተለውን ተግባር እንዲፈጽሙ ደቡብ ኅብረት ያሳስባል።

1. ቀድሞ በአሜሪካንንና በሩዋንዳ መንግሥታት አፍላቂነት፤ በኢ.አ.ድ.ና በተ.መ.ድ ያፀጥታው ምክር ቤት ተደግፎ የቀረበውን የድርድር ኃሣብ ሁለቱም ወገኖች ተቀብለውት ለሠላማዊ ድርድር እንዲዘጋጁ ሆኖ፤ የኤርትራ ጦር ኃይል የያዘውን የኢትዮጵያ መሬት በአስቸኳይ ለቆ እንዲወጣ፤ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲከበርና ለሠላማዊ ውይይቱ መጀመር አመቺ ሁኔታዎች ሁለቱም ሀገሮች እንዲፈጥሩ፤

2. ከላይ የተጠቀሱት አበይት ጉዳዬች እልባት የማያገኙ ከሆነ እንደማንኛውም ነፃ ሀገር፤ የኢትዮ ጵያን ሉዓላዊነት ለማስከበር ሲባል የኢትዮጵያ መንግሥት የሚወስደው እርምጃ ተገቢና አመራጭ የሌለው እንደሆነ እናምናለን።

3. በሁለቱም ሀገሮች መካከል በተከሰተው ግጭት ምክንያት ዜጎችን ከየግዛታቸው በማስወጣቱ ተግባር ሁለቱም ወገኖች የግለሰቦችን ሰብዓዊ መብት ከመጣስ እንዲቆጠቡና የዓለም አቀፍ ደንቦችንና ሥርዓቶችን በተከተለ አኳኋን እንዲፈጽሙ እናስገነዝባለን።

መ. ከጉባዔው የሚጠበቅ:

ደቡብ ኅብረት በሁለቱም የፓሪስ ጉባዔዎች መካከል በነበረው ጊዜ የታቀዱት የትግል ዓላማዎች ምን ያህል ተፈፃሚ ሆነዋል የሚለውን በማጤን ወደ አዲሱና 2ኛው ምዕራፍ የትግል ትልም መሸጋገሩን ይመርጣል። ባለፉት 5 ዓመታት የቱ ጠንካራ፤ የቱ ደግሞ ደካማ ጎናችን እንደነበር ይህ ጉባዔ በሐቅ ማመላከት ይጠበቅበታል። ቀደም ሲል በመግቢያው ላይ እንደተገለፀው ኅብረቱ ፓሪስ በተካሄደው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ኃይሎች ስብሰባ መነሻ ተጎጂም ተጠቃሚም እንደሆነ የሚታወቅ ነው። ተቃዋሚዎቻችን ሰበበኛ ባላንጣዎቻችን የመሆናቸውን ያህል፤ እኛ ደግሞ ፍሬ አልባ በሆነ ጉዳይ መስዋዕት ለመክፈል አንሻም።

ሁልጊዜ በዓላማችን አንፃር ጠቀሜታ ላለው የፖለቲካ ጉዳይ ግንባራችን የማይታጠፍ እንደሆነና ለዚሁ ቅድሚያ የምንሰጥ መሆኑ ከግንዛቤ እንዲገባልን እንወዳለን። የትግል ሥልታችንም ቢሆን ዴሞክራሲያዊ የሆነው ሠላማዊ የትግል መርህ እንደመሆኑ ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በምናደርገው ግንኙነት ወቅት፤ ይኸው ሠላማዊ የትግል መርሃችን እንዲከበርልንና ከግንዛቤ ውስጥ እንዲገባልን እንፈልጋለን።

ሕወሓት/ኢሕአዴግ በሽግግሩ ወቅት ይመራበት የነበረውን ቻርተር ራሱ አሰናክሎ፤ "ነፃ፤ ዴሞክራሲያዊና ሕገመንግሥታዊ ምርጫ" ብሎ የሚጠራውን ብቸኛ ምርጫ ሚያዚያ 29/1987 ዓ.ም. አካሂዶ ሥልጣን ጠቅሎ ቢይዝም፤ በቻርተሩ ጊዜ እንደወተወተው ሁሉ "የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አስከብራለሁ፤ የሕዝቦችን እኩልነት አመጣለሁ፤ልማትና እድገትን በ5 ዓመቱ ዕቅድ እፈጥራለሁ" ቢልም እውን ማድረግ ግን አልተቻለውም። እንዲሁም "ፍትሃዊ አስተዳደር በኢትዮጵያ አሰፍናለሁ" እያለ ከሰባት ዓመታት በላይ ቃል-መግባቱን ባያቋርጥም ጭብጡ ግን ይህን አያመለክትም።

በመሆኑም፡-



1. የሕዝቦች ሰብዓዊ መብት በሚያስደነግጥ ሁኔታ ይጣሳል፤ የዴሞክራሲና የንብረት ባለቤትነት መብት በአሳፋሪ ሁኔታ የገደባል። ባጠቃላይ የዜጎች ሕልውና አስጊ ደረጃ ላይ መሆኑ ታውቆ የጉባዔው አባል ድርጅቶች የጋራ አቋምና የተባበረ የትግል አቅጣጫ በመያዝ ከሕዝቡ ጎን ሆነው የሚታገሉበት ሥልት እንዲቀየስ ለዚህም ኢትዮጵያ አሁን ካለችበት ተጨባጭ ሁኔታ በመነሣት ሁሉም የጉባዔው ተሣታፊ ድርጅቶች በወቅቱ መንግሥት ላይ የሚያካሄዱትንና ያቀዱትን የትጥቅ ትግል ማቋረጡ ይጠበቅባቸዋል።

2. በኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ በተለይ ኢትዮ-ኤርትራ ግጭት አስመልክቶ የኢትዮጵያን ዘላቂ ጥቅም ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በሁለቱ ሀገሮች መካከል የተፈጠረውን የድንበር ግጭት በሠላማዊ አኳኋን በሚቆምበት መላ ላይ እንዲነጋገር፤ ኤርትራ የኢትዮጵያን ግዛትና ሉዓላዊነት መደፈሩን ኅብረቱ ቀጥታ ያወገዘው ቢሆንም የሕወሓት አመራር የሁለቱን ግንኙነት ከኢትዮጵያ ሕዝብና ከሌሎች የመንግሥት አካላት ሰውሮ በዘፈቀደ ሲያካሄድ መሰንበቱ ላፍታም ቢሆን መዘንጋት የለበትም። ይህም በስብሰባው ወቅት በአግባቡ እንዲጤን እንሻለን።

3. ሕወሓት/ኢሕአዴግን ከነእንከኑ ማጋለጥ የሚቻለው የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት እንዲለወጥ በመጠየቅ አይደለም። በነፃ፤ ርዕታዊና ሐቀኛ ምርጫ በዴሞክራሲያዊ መድረክ አይኑ እያየ ለመፋለም ቆርጦ በመነሣት ነው ብለን አምነናል። ስለሆነም በ1992 ዓ.ም. ስለሚደረገው ምርጫ ይህ ጉባዔ በአፅዕኖት ተነጋግሮበት ዓለም-አቀፍ የምርጫ ደረጃ የጠበቀ ዴሞክራሲያዊ የምርጫ ሥርዓት በአገራችን የሚሠራበትን አሠራር በጋራ መንደፍ ይኖርበታል፤

4. ተቋቁመው ያሉት የምርጫ አስፈፃሚ አካላት ከመንግሥት ተፅዕኖ ገለልተኛ አይደሉም። የምርጫ ቦርዱ አባላት የመንግሥት ሹማምንት ሲሆኑ፤ በጀቱ፤ ጽ/ቤቱና የሰው-ኃይሉ ሁሉ በሕወሓት/ኢሕአዴግ የሚመደብ ነው። የምርጫ አስፈፃሚ ኃላፊዎች ሆኑ ሠራተኞች ያለጥርጥር የሕወሓት/ኢሕአዴግ አባላት ወይም ካድሬዎች ናቸው። ስለሆነም፡ የምርጫ፡ አስፈፃሚ፡ ተቋም፡ ከሁሉም፡ ድርጅቶች፡ ተዋጽዖ፡ እንዲቋቋም፡ ጉባዔው፡ አቋም፡ መውሰድ፡ ይኖርበታል።

ስለዚህ ጉባዔው ይህን ተገንዝቦ:-

4.1 በዴሞክራሲያዊ የምርጫ አስፈፃሚ ኢንስቲቲዩሽን ማቋቋም፤
4.2 ከማንም ጫና ነፃ የሆነ የምርጫ አስፈፃሚ አካል መሰየም እና
4.3 የዴሞክራሲያዊ እሴቶችና ሌሎች የምርጫ ቅድመ-ሁኔታዎችና መብቶች በሚሟሉበት ሁኔታዎች ለመደራደር መንግሥት ላይ ጫና ለመፍጠር መንቀሣቀስ ይኖርበታል። እንዲሁም የምርጫው አካሄድ ዴሞክራሲያዊና ሁሉን አሣታፊ ሆኖ፤ በአገሪቱ እንዲሰፍን የምንመኘው ሠላም እንዲሣካ ከሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ጋር ድርድር የሚደረግበት አመች ሁኔታ እንዲፈጠር ስለማድረግ ተነጋግሮ መወሰን ይኖርበታል።

5. የረጅም ጊዜ የሕዝባችን ጥያቄና የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ደካማ ጎን እንደሆነ የሚነገርለት የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች የትግል ትብብር ያለመፈጠር ጉዳይ ነው። ደቡብ ኅብረት ይህ ጉባዔ በዚህ ጉዳይ ላይ ጉልህ ሚና እንዲኖረው የስብሰባውን ተካፋዮች ያሳስባል። በዚህ አኳያ ደቡብ ኅብረት የድርጅት ነፃነቱና የሠላማዊ ትግል መርሁ በማይጣስ ሁኔታ፤ የጋራ ጉዳይ በሆኑ አመለካከቶች ዙሪያ ከሌሎች ፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ለመተባበር ዝግጁ መሆኑን ይገልፃል።

በመጨረሻም፣ ደቡብ ኅብረት ለተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ሆነ በተለይ በሥልጣን ላይ ላለው የወቅቱ መንግሥት ሊያስገነዝብ የሚሻው ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ አሠራር መከተሉ፤ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት በተጨባጭ ሥራ ላይ ማዋሉ እውን ሊሆን የሚችለው፤ ሁሉም ወገኖች የመቻቻል ፖለቲካ መርህ ሲከተሉ እንደሆነ ያምናል። ይህም ማለት የተለያየ ኃሣብ፤ የተለየ የፖለቲካ አቋም፤ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ፖሊሲዎች ያላቸውና እነዚህን የሚያራምዱ የፖለቲካ ድርጅቶች በምርጫ ደንብ መሠረት በሕዝብ እንዲዳኙ ዕድሉ ሊኖርና ሊሰጥ ይገባል ማለት ነው። ዴሞክራሲ ሠላም ነው። ርትዛዊ አስተዳደር የሠላም ዋስትና ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ የሕዝቦች እርካታ የሠላም መሠረት ነው።

ሠላም ከሰብዓዊ ክብር፤ ከዴሞክራሲያዊ ፋይዳዎች መከበርና ከብሄረሰቦች ብሄራዊ መብት ውጭ በተናጠል አይኖርም። የአንዱ አገር መረጋጋት፤ ልማትና ዕድገት ከዚህ በሌላ መንገድ አይገኝም። ከሕዝቦችና ዜጎች ፍላጎት በተፃራሪ የሚኖረው አምባገነንነት ብቻ ነው እንላለን።

ጉባዔው የተሣካ እንዲሆን እንመኛለን!!!
የደኢሕዴኅ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ
ነሐሴ 30 ቀን 1990 ዓ.ም.
አዲስ አበባ ፤ ኢትዮጵያ።